## 2.4. በሥራ ሂደቱ ከተገልጋዩ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች

**1. ለማህበራት ምዝገባ ምስክር ወረቀት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

I. ትክክለኛውን የማህበር ስምና አድራሻ ማህተም ያረፈበትን

II. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ 2 ኮፒ

III. መመስረቻ ጽሑፍ መኖሩ፣

IV. በጠቅላላ ጉባኤ ማኀበሩን የወከሉት ተወካዮች ስምና አድራሻ፣ እንዲሁም የተጠሪነት ደረጃ የሚገልጽ ማስረጃ መያያዙን፣

V. የማህበሩ ማህተም ያረፈበትን ውስጠ ደንብ 2 ኮፒ

VI. የማህበሩን መስራች ኮሚቴ ሪፖርት 2 ኮፒ

VII. የስራ አስፈጻሚ ቦርድ እና ኢንስፔክሽን አባላት ምርጫ ቃለ-ጉባኤ 2 ኮፒ

VIII. የእያንዳንዱ አባላት ሊብሬ 2 ኮፒ

IX. ለማህበሩ ስራ አገልግሎት የሚውል ጽ/ቤት፣ ሰራተኞች፣ ስራ አስኪያጅ እና ሰነዶች መሟላታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣ (ከሥራ ልምድና ከትምህርት ደረጃ ጋር)

X. እያንዳንዱ የተሽከርካሪ ባለንብረት ተሽከርካሪው በሌላ ክልል የቆየ ከሆነ ከነበረበት ክልል ማጣሪያ ደብዳቤ (Clearance) ማቅረብ

XI. በደንቡና መመሪያው መሰረት የአባላትና የተሽከርካሪ ብዛት የተመዘገቡትን ማህተም ያረፈበት ሰነድ 2 ኮፒ ማቅረብ እና

XII. የአገልግሎት ክፍያ ናቸው፡፡ የክፍያ ተመን እንደሚከተለው ነው፡፡

(1) አዲስ የማህበራት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለሚወስዱ፡-

ከ1-50 የተሽከርካሪ ብዛት ብር 1000.00
ከ51-100 ተሽከርካሪ ብዛት ብር 2000.00
ከ101-200 ተሽከርካሪ ብዛት ብር 3000.00
ከ200 በላይ ተሽከርካሪ ብዛት ብር 4000.00

## 2. የማህበራት ምዝገባ ፈቃድ ዕድሳት ለማድረግ የሚሟሉ ቅድመ -ሁኔታዎች

1. የማህበሩ ስምና ትክክለኛ አድራሻ
2. የማህበሩ ተወካይ መታወቂያውንና
   የውክልና ደብዳቤ ከማመልከቻው ጋር ማቅረብ
3. ቅጽ መሙላት
4. ዋናውን የማህበሩን የምዝገባ ፈቃድና የማህበሩን ተሸከርካሪዎች ብዛት የሚገልጽ ማስረጃ
   ማቅረብ እና
5. የአገልግሎት ክፍያ በተመኑ መሰረት መክፈል ናቸው፡፡

ለማህበራት ምዝገባ ፈቃድ ዕድሳት ማስከፈያ ተመን ዝርዝር

ከ1-50 የተሽከርካሪ ብዛት ብር 500.00

ከ51-100 ተሽከርካሪ ብዛት ብር 1000.00

ከ101-200 ተሽከርካሪ ብዛት ብር 1500.00

ከ200 በላይ ተሽከርካሪ ብዛት ብር 2000.00

## 3. ምትክ የማህበራት ምስክር ወረቀት ለመስጠት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ለለውጥ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ወደፊት በሚወጡት ፣ደንቦችና መመሪያዎች የሚገለጽ ይሆናል፡፡

1. የባለጉዳይ ማመልከቻ
2. የማህበሩን ስምና ትክክለኛ አድራሻ የሚገልጽ ማስረጃ
3. የውክልና ደብዳቤ
4. ቅጽ መሙላት
5. ፈቃድ ስለመጥፋቱ የሚገልጽ ማስረጃ
6. የአገልግሎት ክፍያ

# የኦፐሬተርነት ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለመስጠት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ለኦፐሬተርነት ፈቃድ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ /አከፋፈል/ ወደፊት በሚወጡት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሚገለጽ ይሆናል፡፡

- የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ /Road Worthiness Certificate/ ሰርተፊኬት እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ለአገልግሎት በቀረቡት ተሽከርካሪዎች ቁጥር ልክ መሟላቱን፣
- የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ስለሚሠማሩት አሽከርካሪዎች ከፖሊስና ከትራፊክ ፖሊስ ከወንጀል ነፃና ከትራፊክ ፖሊስ የትራፊክ አደጋ ሁኔታ ምስክርነት ማረጋገጫ ደብዳቤ መቅረቡን፣
- የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር ከአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሥራ ሂደት ለአሽከርካሪው የተሰጠ ፈቃድ መኖሩንና ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረቡን፣
- በዘርፉ ለመሰማራት ያመለከተው ኦፕሬተር ከሥራው ጋር አግባብ ያለው ዕውቀትና ልምድ ያለው መሆኑን ለዚህም ማስረጃ ማቅረቡን፣
- አመልካቹ የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ወይም አጠቃላይ ኢንሹራንስ የገባ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረቡ፣
- ሥራውን ለማካሄድ የተደራጀ ቢሮ፣ የሚዛን አገልግሎት፣ የጠፉ ንብረቶች ማከማቻ ቦታ፣ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ መሟላት፣
- የሰው ኃይል ብዛት፣ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት የትምህርት ደረጃና ልምድ የሚገልጽ ማስረጃ መያያዝ አለበት
- አገልግሎቱ የተጠየቀው በድርጅት ከሆነ የድርጅቱ ሕጋዊነት የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው መ/ቤት የተሰጠ ፈቃድ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና ከዞን የሥራ ሂደት ቢሮ ጋር ያለውን ግንኙነት የተመለከቱ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 5. ለመናኸሪያ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማህበራት በመናኸሪያ ውስጥ የሚሰጡት የዕለት ተዕለት ሥራዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### ሀ/ የቢሮ አደረጃጀት

ማንኛውም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖረት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ማህበር ወይም ድርጅት የሚከተሉት መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

- የሥራ አስኪያጅ ቢሮ
- የገንዘብና ንብረት አስተዳደር
- የኦፕሬሽን አፈፃፀም ክትትል ክፍል
- የቲኬት መቁረጫ ቢሮዎች

### ለ/ የሰው ኃይል

የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡና የትራንስፖርት ዘርፍ ለማሳደግ የሚያስችላቸው ሠራተኞች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ማህበር፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሚከተሉት የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ሊኖሩት ይገባል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደቡ | የትምህርት ደረጃ | የሥራ ልምድ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥራ አስኪያጅ | ዲግሪ | 5 ዓመት | ሶሻል ሳይንስና ተመሳሳይ |
| 2 | የገንዘብና ንብረት አስተዳደር | ዲፕሎማ | 2 ዓመት | አካውንቲንግና ተመሳሳይ |
| 3 | የኦፕሬሽን ኃላፊ | ዲፕሎማ | 2 ዓመት | ሶሻል ሳይንስ |
| 4 | የመረጃና ደህንነት ኃላፊ | 10 እና በላይ | 1 ዓመት | |
| 5 | መረጃ አጠናቃሪና ተንታኝ ሠራተኛ | 10ኛ | 1 ዓመት | |

ሐ/ <u>የአገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ሌሎች ስርዓቶች</u>

1. መናኽሪያ ውስጥ በቋሚነት የሚያገለግል ሚዛን፣
2. ዕለታዊ የተሽከርካሪዎች የጉዞ እንቅስቃሴ የሚያሳይ በመናኽሪያ ውስጥ የሚተከል ቦርድ /White board/
3. የተጓዦቹን ጓዝ የማውረድና የማውጣት አገልግሎት መስጫ ስርዓት፣
4. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት፣
5. ኮምፒዩተርና ሌሎች የጽሕፈት መሣሪያዎች፣
6. የጠፉ ዕቃዎች ማከማቻ ስርዓት፣

# 6. <u>ለአገልግሎት የቀረበው ተሽከርካሪ በሚመለከት</u>

## 6.1. <u>የመደበኛ ደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት</u>

- ለዚህ አገልግሎት የሚቀርብ ተሽከርካሪ ለተሣፋሪው መረጃ መስጫ አጋዥ የሆኑ መሣሪያዎች /ማይክራፎኖች፣ የመኪና ቴፕ፣ ስፒከር እና ተንቀሳቃሽ ስልክ እንዲሁም በጉዞ ላይ የተሽከርካሪውን የጉዞ እንቅስቃሴና አቅጣጫ ለመግለጽ የሚያስችል በውስጥና በውጭ የሚታይ ነጭ ሠሌዳ /White board/ ማዘጋጀት፣
- ውኃ ሰማያዊ ዩኒፎርም ለሹፌር፣ ገንዘብ ተቀባይና ረዳቶች እንዲዘጋጅና እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- በወንበሮች ጀርባ ላይ ለእይታ በሚያመች በኘሌት ወይም በማይለቅ ቀለም ቁጥር እንዲፃፍ ወይም እንዲለጠፍ ማድረግ፣
- በተሽከርካሪው ውስጥ የሚቀመጥ የተሟላ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ቁሳቁስና ሣጥን ማሟላት፣
- የእሣት አደጋ መከላከያ ወይም ማጥፊያ መሣሪያ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ፣
- የዕቃ ማስጫኛና መለያ ታግ፣ የጉዞ ትኬትና ደረሰኞች እንዲዘጋጅና በተገቢው ጥቅም ላይ ማዋል፣
- ንፅህናው የተጠበቀ ተሽከርካሪ ማቅረብና ተሽከርካሪው የፀሐይ መከላከያ መጋረጃ ያለው ማድረግ፣
- ቋሚ የዕቃ መመዘኛ ሚዛን እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ በተጨማሪም በጉዞ ላይ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ተንቀሳቃሽ ሚዛን ማዘጋጀት፣

- መነሻና መድረሻ፣ ማረፊያና ማደሪያ ቦታዎችን፣ ለዕረፍት የተመደበውን ጊዜ፣ በተሽከርካሪው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡትን ሠራተኞች ማለትም የአሽከርካሪውን፣ የገንዘብ ተቀባዩንና የረዳቱን ሙሉ ስም እንዲሁም አድራሻ በነጭ ሠሌዳ /White Board/ እና በድምፅ ማጉያ /Mice/ ለተሣፋሪው መግለፅ፣
- የሃሳብ መስጫ ሣጥን አዘጋጅቶ በተሽከርካሪው ውስጥ ለእይታ በሚያመች ስፍራ ማስቀመጥ፣
- ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ደህንነት ምርመራ ወይም ተመሳሳይ ምርመራ በሚገባ ያለፈ መሆኑን፣
- ለተሽከርካሪው የቅድመ ስምሪትና መከላከል ጥገና /Preventive Maintenance/ ሥርዓት የማድረግ ብቃት ያለውና ለዚህም መረጃ በየጊዜው ማቅረብ የሚችል፣
- ተንቀሳቃሽ ስልክ /Wireless Telephone/ ወይም የሬዲዮ ግንኙነት መኖር፣
- መድረሻ ቦታዎች ላይ መድረሻ ሰዓት በቅድሚያ ማሳወቂያ ስርዓት መኖር፣
- ሁሉም መስተዋቶች አደጋ የማያስከትሉ /Safety Glasses/ መሆን አለባቸው።

## 6.2. <u>የመደበኛ ደረጃ 1 የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት</u>

### <u>የተሽከርካሪው ብቃት</u>

ሀ. ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ደህንነት ምርመራ ወይም ተመሳሳይ ምርመራ በሚገባ ያለፈ፣

ለ. ለተሽከርካሪው የቅድመ ስምሪትና መከላከል ጥገና /Preventive Maintenance/ የማድረግ ብቃት ያለውና ለዚህም መረጃ በየጊዜው ማቅረብ የሚችል፣

ሐ. የተሽከርካሪው የፍጥነት፣ የነዳጅ መጠን መቆጣጠሪያና ሌሎች አመላካች መለኪያዎች በትክክል መሥራት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

## የምቾትና የመዝናኛ ሁኔታዎች

### የተጓዥ መቀመጫዎች /Passenger Seats/

1. ሁሉም መቀመጫዎች ምቾት ያላቸውና ቆዳ ወይም ዘመናዊ ጨርቅ የለበሱ መሆን አለባቸው፡፡
2. መደገፊያዎች የጭንቅላት ማሳረፊያ ያላቸውና ወደላይና ወደታች መንቀሳቀስ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3. የተጓዡ ወንበሮች አሠራር እንቅስቃሴን ውጦ የሚያስቀሩ መሆን አለባቸው፡፡
4. የአንድ ተሳፋሪ መቀመጫ 400ሚ.ሜ X 400ሚ.ሜ መሆን አለበት፡፡
5. ከፊትና ከኋላ ባሉት ወንበሮች መካከል ያለው ርቀት 785ሚ.ሜ ማነስ የለበትም፡፡
6. መተላለፊያው 350 mm ማነስ የለበትም፡፡

### የአውቶቡስ ውስጥ መስተንግዶ /In bus-Entertainment/

1. TV/DVD ሲስተም ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የተዘጋጁ ምግቦችና የቀዝቃዛ መጠጥ አገልግሎት መስጫ ሁኔታ መኖር አለበት፡፡
3. አሽከርካሪው፣ ረዳቱና ገንዘብ ተቀባዩ መነጋገሪያ ሥርዓት /Communication System/ ሊኖረው ይገባል፡፡
4. መልዕክት ለተጓዦች ማስተላለፊያ መሣሪያ /Mice/ ሊገጠምለት ይገባል፡፡
5. የአውቶቡስ ወለል ምንጣፍ የተደረገለት መሆን አለበት፡፡

#### መገናኛ ስርዓት /Communication System/

ሀ. ተንቀሳቃሽ ስልክ /Wireless Telephone/ ወይም የሬዲዮ ግንኙነት መኖር፣

ለ. መድረሻ ቦታዎች ላይ መድረሻ ሰዓት በቅድሚያ ማሳወቂያ ስርዓት መኖር፣

#### መስኮቶችና መስታዋቶች

ሀ. ሁሉም መስተዋቶች አደጋ የማያስከትሉ /Safety Glasses/ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. በአደጋ ጊዜ መውጫ የሚሆኑ መስኮቶች ሊኖረው ይገባል፡፡

#### የደህንነት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያዎች

ሀ. ሁሉም መቀመጫዎች አግባብነት ያላቸው የደህንነት ቀበቶ የተገጠመላቸው መሆን አለባቸው፡፡

ለ. የተሽከርካሪው ዝናብ መጥረጊያ ውሃ መርጫና ሦስት የፍጥነት ደረጃዎች ያሉት፣

ሐ. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያዎች ያሉት፣

መ. የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

**ሌሎች**

ሀ. ውኃ ሰማያዊ ዩኒፎርም ለሹፌር፣ ገንዘብ ተቀባይና ረዳቶች እንዲዘጋጅና እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

ለ. በወንበሮች ጀርባ ላይ ለእይታ በሚያመች በኘሌት ወይም በማይለቅ ቀለም ቁጥር እንዲፃፍ ወይም እንዲለጠፍ ማድረግ፣

ሐ. የዕቃ ማስጫኛና መለያ ታግ፣ የጉዞ ትኬትና ደረሰኞች እንዲዘጋጅና በተገቢው ጥቅም ላይ ማዋል፣

መ. ንፅህናው የተጠበቀ ተሽከርካሪ ማቅረብና ተሽከርካሪው የፀሐይ መከላከያ መጋረጃ ያለው፣

ሠ. ቋሚ የዕቃ መመዘኛ ሚዛን እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ በተጨማሪም በጉዞ ላይ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ተንቀሳቃሽ ሚዛን ማዘጋጀት፣

ረ. መነሻና መድረሻ፣ ማረፊያና ማደሪያ ቦታዎችን ለዕረፍት የተመደበውን ጊዜ በተሽከርካሪው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡትን ሠራተኞች ማለትም የአሽከርካሪውን፣ የገንዘብ ተቀባዩንና የረዳቱን ሙሉ ስም እንዲሁም አድራሻ የያዘ ማስታወቂያ ሊታይ በሚችል ጉልህ ጽሁፍ አዘጋጅቶ መለጠፍ፣

ሰ. የሃሳብ መስጫ ሣጥን አዘጋጅቶ በተሽከርካሪው ለእይታ በሚያመች ስፍራ ማስቀመጥ፣

## 6.3. <u>የልዩ ትራንስፖርት አገልግሎት</u>

**<u>የተሽከርካሪው ብቃት</u>**

ሀ. ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ደህንነት ምርመራ ወይም ተመሳሳይ ምርመራ በሚገባ ያለፈ፣

ለ. ለተሽከርካሪው መከላከል ጥገና /Preventive Maintenance/ የማድረግ ብቃት ያለውና ለዚህም መረጃ በየጊዜው ማቅረብ የሚችል፣

ሐ. የተሽከርካሪው የፍጥነት፣ የነዳጅ መጠን መቆጣጠሪያና ሌሎች አመላካች መሳሪያዎች በትክክል መሥራት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

## የምቾትና የመዝናኛ ሁኔታዎች

### የተጓዥ መቀመጫዎች /Passenger Seats/

1. እያንዳንዱ መቀመጫ ከጐኑ ያለው መቀመጫ ሳይነካ ወደፊትና ወደኋላ በተፈለገው መጠን መንቀሳቀስ የሚችል መሆን ይኖርበታል /Reclining Seat/
2. ሁሉም መቀመጫዎች ምቾት ያላቸውና ቆዳ ወይም ዘመናዊ ጨርቅ የለበሱ መሆን አለባቸው፡፡
3. መደገፊያዎች የጭንቅላት ማሳረፊያ ያላቸውና ወደላይና ወደታች መንቀሳቀስ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
4. የተጓዡ ወንበሮች አሠራር እንቅስቃሴን ውጦ የሚያስቀሩ መሆን አለባቸው፡፡
5. የአንድ ተሳፋሪ መቀመጫ 450ሚ.ሜ X 450ሚ.ሜ መሆን አለበት፡፡
6. ከፊትና ከኋላ ባሉት ወንበሮች መካከል ያለው ርዝመት 880ሚ.ሜ ማነስ የለበትም፡፡
7. ከግራና ቀኝ ባሉት ወንበሮች መካከል /መተላለፊያው/ 550 ሚ.ሜ ማነስ የለበትም፡፡
8. ወንበሮች ታጣፊ የእጅ ማሣረፊያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### የአውቶቡስ ውስጥ መስተንግዶ /In bus-Entertainment/

1. TV/DVD ሲስተም ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የተዘጋጁ ምግቦችና የቀዝቃዛ መጠጥ አገልግሎት መስጫ ሁኔታ መኖር አለበት፡፡
3. አሽከርካሪው ረዳቱ መነጋገሪያ ሥርዓት /Communication System/ ሊኖረው ይገባል፡፡
4. መልዕክት ለተጓዦች ማስተላለፊያ መሣሪያ /Mice/ ሊገጠምለት ይገባል፡፡
5. የአውቶቡስ ወለል የማያንሸራትት ምንጣፍ የተደረገለት መሆን አለበት፡፡
6. የተሽከርካሪው የማሞቂያና ማቀዝቀዣ /AC/ ለእያንዳንዱ መቀመጫ ላይ ያለው፣

**መገናኛ ስርዓት /Communication System/**

ሀ/ ተንቀሳቃሽ ስልክ /Wireless Telephone/ ወይም የሬዲዮ ግንኙነት መኖር፣

**መስኮቶችና መስታዋቶች**

ሀ. ሁሉም መስተዋቶች አደጋ የማያስከትሉ /Safety Glasses/ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. በአደጋ ጊዜ መውጫ የሚሆኑ መስኮቶች /Emergency Exit Window/ ሊኖረው ይገባል፡፡

**የደህንነት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያዎች**

ሀ/ ሁሉም መቀመጫዎች አግባብነት ያላቸው የደህንነት ቀበቶ የተገጠመላቸው መሆን አለባቸው፡፡

ለ/ የተሽከርካሪው ዝናብ መጥረጊያ ውሃ መርጫና ሦስት የፍጥነት ደረጃዎች ያሉት፣

ሐ/ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያዎች ያሉት፣

መ/ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፣

ሠ/ ከተሽከርካሪው ውስጥ ግድግዳ ጋር የተያያዘ ወይም በወንበሮች መካከል የተተከሉ በእጅ የሚጨበጡ መደገፊያዎች /Handrail/ ያለው፣

በመናኸሪያ የትራንስፖርት አገልግሎቶች መረጃና ክትትልና ባለሙያ ከዚህ በላይ በ"ሀ" እና "ለ" እና "ሐ" ሥር የተገለፁት ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና ኦፕሬተሩ ያቀረበው የስምሪት ኘሮግራም ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪም በሥራ መዘርዝሩ ላይ የተቀመጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡